# መዘጋጀት ለ Pre-K

Ready for Pre-K!

**Pre-K መጀመር አስደሳች ጊዜ ነው!**
ለልጆችም ሆነ ለቤተሰቦች እንደ ትልቅ ሽግግር ሊሰማቸው ይችላል። ሁሉም ሰው በትምህርት አመቱ ጥሩ ጅምር እንዲኖረው የሚያግዙ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች እንሆ።



## ለመርዳት ምን ማድረግ ይችላሉ?

### 1። መደበኛ ተግባሮችዎን ይለማመዱ

ሁሉም ሰው ለመስተካከል ጊዜ እንዲኖረው፣ ትምህርት ከመጀመሩ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ የጠዋት ተግባርዎን ይለማመዱ። እርስዎ እና ልጅዎ በየቀኑ ስንት ሰዐት መነሳት ያስፈልግዎታል? በቂ እንቅልፍ ለማግኘት ስንት ሰዓት ላይ መተኛት አለባቸው? የ3- እና የ4- አመት ህጻናት በየቀኑ ከ10-13 ሰዓታት መተኛት እንደሚያስፈልጋቸው ያውቃሉ (የቀን እንቅልፍን ጨምሮ)? ለልጅዎ የጠዋት ተግባር የስዕል መርሃ ግብር መሳል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ:- ተነስ/ሽ። ልበስ/ሽ። ቁርስ ብላ/ዪ። ጥርስህን/ሽን ቦርሽ/ሺ። ጫማ አድርግ/ጊ። ለመሄድ ጊዜው ነው!

**ድህረገጻችን ይጎብኙ**

# የመጀመሪያ ሂሳብ ክህሎቶችን ለመደገፍ ጠቃሚ ምክሮች

## 2። የስንብት ስነ ስርዐት መፍጠር

ከልጅዎ ጋር ይህንን ስርዐት ተለማመዱ፣ በዚህም ሁለታችሁም በምትወርዱበት ጊዜ ስለሚጠብቃችሁ ነገር እርግጠኝነት ይሰማዎታል። ለምሳሌ፣ “አንድ የድብ መተቃቀፍ፣ ሁለት የቢራቢሮ መሳሳም እናደርጋለን ከዚያም ደና ሁን እንላለን። በቀኑ መጨረሻ ልወስድህ/ሽ እመጣለሁ!”





## 3። ትምህርት ቤት መጎብኘት

በበጋ የልጅዎን ትምህርት ቤት ይጎብኙ። ለልጅዎ ምን እንደሚመስል ለማስታወስ የፊት መግቢያውን እና የመጫወቻ ቦታውን ፎቶ ያንሱ። እርስዎ ሊሳተፉባቸው የሚችሏቸው የበጋ ክፍት ቤቶች ወይም የPre-K የጨዋታ ቀኖች መኖራቸውን ለማየት ትምህርት ቤትዎን ያነጋግሩ።

## 4 አስተማሪዎን ያግኙ

ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን በፊት ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ለመገናኘት እድል ያግኙ። ይህ በመጫወቻ ቀን፣ በቤት ጉብኝት፣ ወይም በቪዲዮ ጥሪ ወቅት ሊከሰት ይችላል! የአስተማሪውን ስም እና ምን እንደሚመስሉ ማወቅ አንዳንድ የልጅዎን ጭንቀት ለማስታገስ ይረዳል። ስለ ልጅዎ እና ቤተሰብዎ አንዳንድ አስደሳች እውነታዎችን ማጋራትዎን እርግጠኛ ይሁኑ!




## 5. ታሪኮችን ያንብቡ

ትምህርት ቤት መጀመርን የሚመለከቱ ታሪኮችን ማንበብ ልጅዎ ምን እንደሚጠብቀው እንዲያውቅ ለመርዳት እና ምን ሊሰማቸው እንደሚችል ውይይቶችን ለመጀመር ጥሩ መንገድ ነው።

DCPS የቅድመ ልጅነት ትምህርት

@dcpsearlychildhood

readyforprek.org